# ከእኛ ዘንድ ወጡ ግን ከኛ ዘንድ አልነበሩም
# ዳግማዊ ወክ አውት

በልጅግ አሊ

"ከእኛ ዘንድ ወጡ፣ ዳሩ ግን ከኛ ወገን አልነበሩም።ከእኛስ ወገንስ ቢሆኑ ከእኛ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር፣ ነገር ግን ሁሉ ከኛ ወገን እንዳልሆኑ ይገልጹ ዘንድ ወጡ።"

ዮሐ. መፅ.2፣19

ወክ አውት (Walk Out) ቀጥተኛ ትርጉሙ ስብሰባን ወይም ጉባዔን ረግጦ በአፈንጋጭነት መውጣት ነው።ምንም የባዕድ ቋንቋ ቢሆንም በአሁኑ በሃገራችንን ፖለቲካ አዲስ ትርጓሜ እያያዘ ስለመጣ በዛሬው ፅሁፌ ላይ እንድየቀምበት አንባቢያንን ቀደም ብዬ እጠይቃለሁ ።

በሰሜን አሜሪካ በዋሽንግቶን ከተማ በተደረገው የእግር ኳስ ጨዋታን አስታኮ ብዙ ዝግጅቶችም ይካሄዳሉ።ከነዚህም ዝግጅቶች ውስጥ ደብዛቸው በወያኔ ለጠፋ እንደነ ጸጋዬ ደብተራው አይነት ታጋዮች በተደረገው ሲንፖዚየም እና የቀድሞ የኢሕአፓ አባላት የሚገናኙበት ዝግጅት ላይ ለመገኘት እድል ገጥሞኝ ነበር።

በአሲንባ የፓልቶክ ክፍል አቀናባሪነት የተዘጋጀው ሲንፖዚየም በጥሩ ሁኔታ ተከታትየዋለሁ። ይህ ድምፅ ለሌላቸው ድምፅ የመሆኑ እንቅስቃሴ በአንድ ዶክተር አሳሳቢነት የተጀመረ ቢሆንም በተቀነባበረ ሁኔታ የታሰበለትን ዓላማ እንዲመታ አስተዋፅኦ ላበረከቱት ሁሉ አድናቆቴን እገልፃለሁ።

ለዛሬው ፅሁፌ መነሻ የሆነው ግን ደግሞ ሌላ የተሳተፍኩበት ዝግጅት ነው።ይህም የቀድሞ የኢሕአፓ አባላትን ለማገናኘት የሚዘጋጀው ዝግጅት ነው።በቦታው በመገኘት ያየሁትን ለመመስከር እድሉን ስጠብቅ በድህረ ገጽዎች ላይ ከፎቶ ማስረጃ ጋር ያለውን ተመለከትኩ።ቢሆንም እኔም የግሌን ምስክርነት መስጠት ስለፈልግሁ ይህንን ፅሁፍ አዘጋጀሁ።

መቼስ ዘንድሮ ወክ አውት የተለመደ ክስተት እየሆነ መጥቷል።የዘንድሮ ወክ አውት ትርጉሙ ምን እንደሆነ እንደኔ ግራ የተጋባችሁ አትጠፉም። ትርጉሙ ግን የልዩነት አሳቦችን ትፋጥርና ብዙሃኑ ከአንተ ጋር አለመሆኑን ስታውቅ ሰው አይኝ አላየኝ እያልክ እራስህን ደብቀህ ፣የቻልከውን ጉዳት አድርሰህ ፣ ጨለማን ተገን አድርገህ ጥፋና ሌሎች ምክንያቶች ፈልገህ ቶሎ መግለጫ አውጣ የሚል የአንጃኞች መመሪያ ነው። እኔ በበኩሌ ለዘንድሮው ወክ አውት ከዚህ የተሻለ ሌላ ትርጉም ላገኝለት አልቻልኩም።

በቅርብ ግዜ ሁለት ተከታታይ ወክ አውቶችን ታዝቤያለሁ።ቀዳማዊ ወክ አውት የምለው ከኢሕአፓ አስቸኳይ ጉባዔ አንጃኞች የተጠራን ጉባዔ በመርገጥ ከውይይት የፈረጠጡበት ሲሆን፣ ዳግማዊ ወክ አውት የምለው ደግሞ በዋሽንግተን በተደረገው የቀደሞ የኢሕአፓ አባላት ለማገናኘት የሰሜን አሜሪካ እግር ኳስ ጨዋታን አስታኮ ከሚደረገው ዝግጅት ላይ የአንጃው መሪዎች ሰው አየን

አላየን ብለው ማንንም ሳይሰናበቱ ሾልከው እንደለመዱት ጨለማን ተገን አድርገው ከዝግጅቱ ወክ አውት ያደረጉበትን ነው።

በቅርብ ግዜ የአንጃው መሪዎች የመጀመሪያውን ወክ አውት ሲያደርጉ ከልቤ በጣም ታላቅ ሃዘን ተሰምቶኝ ነበር። እንደው ለምን? ብዬ እራሴንም ጠይቄ ነበር። ከኛው ጋር የነበሩ፣የኛ ስቃይ የሚሰማቸው፣መከራችን መከራቸው የሆነ፣ሃዘናችን ሃዘናቸው ነው በሚል እምነት በውስጤ ይኖር ስለነበር ሃዘኑም ጠንክሮብኝ ነበር።በተለይ ደግሞ ብዙዎቻችንን የምንጋራው የጋራ ሕመም በሰውነታችን ላይ የደረሰው መከራ ፣ ከአጠገባችን ያጣናቸው ጓዶቻችንን ፣ ታሪካችን የጋራ ነው ብዬ ስለማምን የተሰዉ ጓዶችን የማስታወስ ሃላፊነትን አብረን እንወጣለን ብዬም ገምቼ ነበር።እኔ በበኩሌ አንጃዎቹ እነዛ በወጣትነታቸው የተቀጠፉትን ወጣቶች የሚያስታውሱ፣ ከልባቸው ለሃገራቸው እድገት ሲሉ መሰዋዕትነት የከፈሉ መሆናቸውን የሚያምኑም፣ ይመስሉኝም ነበር።

ከወክ አውት ቀዳማይና ዳግማይ ክስተት በኋላ አለመሆኑን በተግባር በተደጋጋሚ ያየሁት ሰለሆነ ከማንም ምንም መረጃ አልፈልግም። በዚህ የቀድሞ አባላት በሚገኙበት ስብሰባ ላይ አንድ የንፁሃንን ደም ያፈሰሰ ግለሰብ መጋበዝ ምንኛ በተሰውት ወጣቶች ላይ ማሾፍ መሆኑን ያልተረዳ ካለ የሥልጣን ፍቅር ዐይኑን የሸበበው ግዑዝ ፍጡር ብቻ ነው።የዘንድሮውን የቀድሞ የኢሕአፓ አባላት ዝግጅትን የበጠበጠው አረጋዊ በአንጃው መሪዎች በመጋበዙ ነው። አረጋዊ በተደጋጋሚ እንደተገለፀው በንፁሃኑ ደም ተጠያቂ ከሆኑት ግለሰቦች መካከል አንዱ ነው።ይህ ግለሰብ ለተሰራው ጥፋት እስካሁን በሕዝብ ፊት ይቅርታን ያልጠየቀ ሲሆን አልፎ ተርፎ የተሰውትን ወጣቶችን ለመወንጀል የሚሞክርም ነው። ይህንን ግለሰብ ታዲያ አንጃዎቹ ሲጋብዙት ይህንን ሳያውቁት ነው ብዬ አላምንም። ሁኔታውን ከማናችንም በላይ ይረዱታል። ሁኔታው ግን የዮሐንስ መልክት ከኛ ወገን እንዳልሆኑ ይገልጹ ዘንድ ወጡ እንደሚለው ነው።ከኛ አለመሆናቸውንም ቁርጥ አድርገን እንድንረዳው የሚደርጉት ያላሰለሰ ጥረት ነው ብዬ አምናለሁ።

አንዳንድ የቀድሞ አባላት የኢሕአፓን አባልነት እርግፍ አርገው የተውበት ዋናው ምክንያት እንዴት ከእነ አረጋዊ ፣ ከነ ነገደ ጋር ሕብረት ይፈጠራል? በማለት ነው።ይህ ዝግጅት ደግሞ እንደዚህ አይነት አመለካከት ያላቸውንም ጭምር ያካትታል።ታዲያ እዚህ ዝግጅት ላይ አረጋዊን ይዞ መምጣት፣ ምውታንን ለማበሳጨት ወይስ የተሰውበትን ተግባር ለማዋረድ ነው? የአንጃው መሪዎች ስልጣን ለማግኘት፣ አንዴ አውሮፓ ፣ አንዴ አሜሪካ፣ይሽከርከሩ እንጂ ደግሞ የምን የተሰው ጓዶች ማስታወስ ነው? የምን ደግሞ ድምፅ ለሌላቸው ድምፅ መሆን ነው? ይህንን ከነእርሱ የሚጠብቅ ካለ ከእባብ እንቁላል እርግብ እንደመጠበቅ ነው።

ዛሬ ይህንን የቀድሞ አባላት ዝግጅት ለአንጃዎችና ለነ አረጋዊ አዲሱ ሠርጋቸው የአንጃው መሪዎች የቤተ ዘመድ ቅልቅል ሊያደርጉት ቢሞክሩም ብዙሃኑ እንቢኝ በማለቱ ምክንያት የአንጀው መሪዎች እንደለመደባቸው ሳይሰናበቱ በተደበቀ ሁኔታ ዳግማዊ ወክ አውት አድርገዋል። ብዙሃን አልነበሩምና ትተው ሄደዋል።

የተፈፀመው ሁኔታ አሳዛኝና አሳፋሪ ብቻ አደለም። ሁኔታው ሌሎች ጥያቄዎችንም የሚያስነሳ ነው። እነ መርሻ በዚህ በትግሉ ውስጥ የተሰዉ ግለሰቦችን ለማስታውስ በሚደረገው ዝግጅት ውስጥ አረጋዊ በርሂን ይዘው መምጣታቸው በፅሁፌ መግቢያ ላይ ከመጀመሪያው የዮሃንስ መልዕክት ምዕራፍ ሁለት ቁጥር አስራ ዘጠኝ ላይ የጠቀስኩትን እንዳስታውስ ያደርገኛል።እውን ይህንን ያደረጉት ግለሰቦች ከኢሕአፓ ጋር ነበሩ? እውን ጌታቸው፤ መርሻ በወያኔ ደብዛቸው ለጠፉ ታጋዮች ልባቸው ይደማል? እኔን አይመስለኝም። ከእኛ ዘንድ ወጡ፣ ዳሩ ግን ከኛ ወገን አልነበሩም።

በዚህ ዝግጅት አጠገቤ የተቀመጠው ግለሰብ ከወያኔ ጋር በተደረገው ጦርነት የሚወዳቸውን ጓዶቹን ያጣ ነበር። ሊያስታውሳቸው የመጣውም እኒዚህን ጓዶቹን ነው።ገና አዲስ ሃዘን ይመስል

ሁኔታው ፊቱ ላይ ይነበባል። የአረጋዊን በዚህ ዝግጅት መገኘትን ከብዙዎቻችንን የበለጠ አምርሮ ይቃወም ነበር። ታዲያ ያ የተለመደ የመርሻ የለበጣ ፈገግታ ይህንን ለብዙ ዓመታት ሃዝን ልቡን ላቆሰለው ግለሰብ የሚሰጠው መልዕክት አንድ ነው። እሱም "ከእኛስ ወገንስ ቢሆኑ ከእኛ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር" የሚለውን ነው።

ለመሆኑ አንዳንዶቻችሁን የአንጃው ደጋፊዎችን ልጠይቃችሁ።በሰው ቁስል እንጨት ሰደድበት ካልሆነ በቀር በየአካባቢያችን የነበሩ ፋሽሽቶች ቢጋበዙ ኖሮ አናብድም ነበር? ጎበዝ በአንድ እራስ ሁለት ምላስ አንሁን። ትላንት አብረን እናለቅስላቸው ለነበሩት ወጣቶችን ዛሬ በአዲስ ዘፋን አዲስ ዳንኪራ ልንረግጥ አይገባም። ትላንት ራዲዮናችሁ ስዬን ሲያሞግስ ፣ ትላንት መሪዎቻችሁ ቀይ ሽብርን ከሚደግፉ ክፍል ሄደው የኢሕአፓን ታሪክ ሲያሰድቡ፣ዛሬ ደግሞ አረጋዊን በዚህ ዝግጅት ሲጋብዙ የሚሰጡዋችሁ ምክንያት ያው የተለመደውን ነው።እውነታው ግን ለሥልጣን መፈናጠጫነት እየተጠቀሙባችሁ ነው።እኔ እንደ ፒላጦስ ከደሙ ንፁህ ነን ብላችሁ እጃችንን በሕዝብ ፊት ልትታጠቡ ይገባል። አልያ ግን የእነዚያ የጓዶቻችንን አጥንት እሾክ ሆኖ በየቦታው ሲወጋችሁ ይከርማል።

ብዙ የአንጃው ደጋፊዎች ኢሕአፓ ከእነዚህ ግለሰቦች ጋር ግንባር ፈጥሮአልና አሁን አረጋዊን መጋበዛችን ስህተት የለውም ብለው ይናገራሉ።አዎ ልክ ነው ኢሕአፓ ግንባር ፈጥሮአል።ግን ይህ ዝግጅት በኢሕአፓ የተዘጋጀ አደለም። ኢሕአፓም የሚቆጣረው አደለም።ዝግጅቱ ውስጥ የነበሩት ሁሉም የአሁን የኢሕአፓ አባላትም አደሉም።ይህ የተለመደ የተሳሳተ የአንጃ ስሌታችሁ ሁል ግዜ ለተደጋገመ ስህተት ያጋልጣችኋል።በቀዳማይ ወክ አውት እናገኛለን ብላችሁ የነበረውን የቀድሞ አባላት ድጋፍ አጥታችኋል።በዳግማዊ ዎክ አውት በቅሌት በጭለማ ሳትሰናበቱ ወጥታችኋል። በሳልሳይ ወክ አውት የሚጠብቃችሁን አላውቅም ግን እንደለመዳችሁት አንድ ቅሌት ይዛችሁ እንደምትመጡ አልጠራጠርም።

ለነገሩማ ብትፈልጉ የፈለጋችሁትን በሉኝና አሁን በነአረጋዊ የተመሰረተው ጥምረት የሚባለውን በጣም ነው የምደግፈው። ትዴት (TAND) ፣ መኢሶንን ፣ ዴኢህአፓን የሚባሉትን ስሞች ከአለም ካጠፉቸው ሌላ ምንም የምፈልገው ጉዳይ ከጥምረቱ አይኖርምም፣ አልጠብቅምም። ስለቱ ደረስ ብዬም መኩራራቴ አይቀርም። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በደም የተበከሉ ድርጅቶችን በጥምረት ስም ይሁን በውህደት ስም አስከፊው ስማቸው ከኢትዮጲያ ፖለቲካ ከጠፋ ለብዝዎቻችን የተወሰነ የደም ካሳ ብዬ አምናለሁ።

እኔ ግን ይህ በዝግጅቱ ምክንያት ያየሁትን ዳግማዊ ወክ አውት በማየቴ ደስተኛ ነኝ። የአንጃው መሪዎች ሾልከው ሲሄዱ ስለተመለከትኩ ደስተኛ ነኝ።የቀድሞ የኢሕአፓ አባላት የተሰው ጓዶቻቸውን ስላልረሱ ደስተኛ ነኝ። የአንጃው መሪዎች ሲሸማቀቁ በማየቴ ደስተኛ ነኝ። የአንጃው ተንኮል በመክሸፉ ደስተኛ ነኝ። የሕዝብ አይንን ፣ የሕዝብን ቁጣ ፈርቶ እሰከመቼ? ተከብሮ በተኖረበት አገር ተሸማቆ በስተመጨረሻ እንዲህ መሆን ለምን?

በዚህ ስብስብ ላይ የእናታችን ወደ ስብሰባው መግባትና የክብር አቀባበል መደረግ ለአንጃ መሪዎች የመልዕክት ጥሪ አስተላልፎአል። ይኸውም የህዝብ ፍቅር ለአላማ ፅናት የሚሰጥ እንጂ ለአድርባይነት እንዳልሆነ የአንጃው መሪዎች ሊመለከቱት ችለዋል። በሕዝብ መከበር በአቋም እንጂ ወደ ጠባባት በማዝገም እንዳልሆነ ተመልክተውታል።

ዳግማዊ ዎክ አውት ፣ በሳልሳዊ እንደሚደገም ደግሞ ጥርጥር የለኝም። ዛሬ በአለም የሚገኙ የቀድሞ የኢሕአፓ አባላትና በተሰው ጓዶቻቸው ላይ የሚፈፀመውን ደባ ይዋጉታል ብዬ አምናለሁ።

ድል ለኢትዮጲያ ህዝብ

በልጅግ አሊ
ሀምሌ 2000
Beljigali@beljigali.com